# በአገር ውስጥ በሚመረቱ ዕቃዎች ላይ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበትን ጊዜ ለማሳወቅ የወጣ መመሪያ ቁጥር 18/2001

በአገር ውስጥ በሚመረቱ ዕቃዎች ላይ የኤክሳይዝ ታክስ መክፈያ ጊዜን በግልጽ ማስቀመጡ ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ፣

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 307/1995 አንቀጽ 35 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህ የአፈጻጸም መመሪያ ወጥቷል።

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ መመሪያ "በአገር ውስጥ በሚመረቱ ዕቃዎች ላይ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበትን ጊዜ ለማሳወቅ የወጣ መመሪያ ቁጥር 18/2001" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

   "አዋጅ" ማለት የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 307/1995 ነው።

3. **የኤክሳይዝ ታክስ መክፈያ ጊዜ**

   1. በአዋጁ አንቀጽ 6(2) (ሀ) (2) መሠረት ኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸው ዕቃዎች በአገር ውስጥ ሲመረቱ ከተመረቱበት ቀን ጀምሮ በ30 ቀናት ውስጥ ኤክሳይዝ ታክስ ይከፈልባቸዋል።
   2. ለዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) አፈጻጸም በዕቃዎቹ ላይ ታክሱ የሚከፈበት ጊዜ ዕቃዎቹ ከተመረቱበት ወር ቀጥሎ ባሉት 30 ቀናት ውስጥ ነው።

4. **የተሻሩ መመሪያዎች**

   ይህ መመሪያ በሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት የነበሩ መመሪያዎች በዚህ መመሪያ ተተክተዋል።

5. **መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ**

   ይህ መመሪያ በባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ተፈርሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል።

አዲስ አበባ ------------- ቀን 2001 ዓ.ም.

መላኩ ፈንታ
የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
ዋና ዳይሬክተር

# ከተርንኦቨር ታክስ ነፃ የሆኑ ምርቶችንና አገልግሎቶችን ለማሳወቅ የወጣ መመሪያ----------/2001

ምርቶችና አገልግሎቶች ካላቸው ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ አንጻር ከታክስ ነፃ ሆነው መቅረባቸው በዋጋ ረገድ የሚኖረውን ተጽዕኖ ማርገብ ስለሚቻል፣

እንደየወቅቱ ሁኔታ እየታየም በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ተጨማሪ ምርቶችና አገልግሎቶች ከታክስ ነጻ የሚደረጉ በመሆኑ፣

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በሚኒስትሮች ምክር ቤት የተጨማሪ እሴት ታክስ ደንብ ቁጥር 79/1995 አንቀጽ 39 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህ የአፈጻጸም መመሪያ ወጥቷል።

## 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "ከተርንኦቨር ታክስ ነጻ የሆኑ ዕቃዎችንና አገልግሎቶችን ለማሳወቅ የወጣ መመሪያ ቁጥር ---------/2001" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## 2. ከተርንኦቨር ታክስ ነፃ የሆኑ ምርቶችና አገልግሎቶች

1. በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 255/1994 አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ (2) ላይ የተመለከቱት ምርቶችና አገልግሎቶች ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነፃ ናቸው።
2. በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በተሰጠው ሥልጣን መሠረት በየወቅቱ ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነጻ የሚደረጉ ምርቶችና አገልግሎቶች ይኖራሉ።
3. ምርቶችና አገልግሎቶች ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነፃ ሲደረጉ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታቸው እየታየ በመሆኑ፣ ከታክሱ ነፃ የሆኑ ምርቶች በሙሉ ከተርንኦቨር ታክስም ነፃ ይሆናሉ።

## 3. የተሻሩ መመሪያዎች

ይህ መመሪያ በሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት የነበሩ መመሪያዎች በዚህ መመሪያ ተተክተዋል።

## 4. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ተፈርሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል።

አዲስ አበባ ------------ ቀን 2001 ዓ.ም.

መላኩ ፈንታ
የገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
ዋና ዳይሬክተር